# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
## *Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)*
(አንድነት/United)


የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ. ም
March 3, 2016

# ዓለምአቀፍ የሴቶችን ቀን ስንዘክር

ዓለምአቀፍ የሴቶችን ቀን ስንዘክር፣ ለሴቶች እኩልነትና ለማንነት ለተደረገው ትግል መንስዔ የሆኑትን በጥቂቱ ስናስታውስ፣ ከ19ኛው ክፍለ-ዘመን መጨረሻና ከ20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን መግቢያ ጀምሮ በሰሜን አሜሪካና በአውሮጳ የተቀጣጠሉት የላብ-አደሩ እንቅስቃሴዎች ያደረጉትን አስተዋጽዖ መሠረትነት ባለመዘንጋት መሆን ይገባዋል። በዓለም ሠርቶ-አደሮች ተጋድሎ ዓለምአቀፍ የሴቶች ቀን በዓለም ዙሪያ በአንዳንድ ባደጉና በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ሲታሰብ ኖሯል። የተባበሩት መንግሥታትም ለዓለምአቀፍ የሴቶች እንቅስቃሴ ሴቶች በኅብረተ-ሰቡ ውስጥ በኤኮኖሚና በፖለቲካ ሊኖራቸው ስለሚገባው የመብት ጥያቄ የሚያደርገውን አጋርነትም አንዘነጋም።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሴቶች የመብትና የእኩልነት ጥያቄ በማደግ ላይ ከሚገኙ አገሮች ሴቶች መብቶችና እኩልነት በጣም ባነሰ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የተባበሩት መንግሥታት ጥናት ያመለክታል። በጥናቱ መሠረት፣ "... አገሪቱ ከፍተኛ ቁጥር (ከ100,000 ውስጥ 850ዎቹ) በወሊድ የሚሞቱባት፤ ገና የ14 ሊጋ ዕድሜ ላይ ካሉ በርካታ ሕፃናት ውስጥ 50 በመቶው ሴቶች በHIV/AIDS የተለከፉባትና (ከ230,000 በላይ) ይህ ቁጥርም በየዓመቱ በ80,000 ሺህ እየጨመረ የሚሄድባት" ሕዝብ የሚኖርባት አገር ናት ይላል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ወጣት እህቶቻችን ለአቅመ-ሔዋን ከመድረሳቸው በፊት ያለዕድሜያቸው በትዳር ዓለም ውስጥ እንዲገቡም ሆነዋል። በኀርምሳ እየተደፈሩ የሚያረግዙት ሕፃናት ቁጥር በጣም ብዙ ነው። ተምረው ሥራ በማጣት በሴተኛ አዳሪነት ተሰማርተው ሰውነታቸውን ሸጠው የሚተዳደሩት እህቶቻችን ቁጥርም በትንሹ የሚገመት አይደለም። በዚህ ሥራ የተሰማሩ በርካታ እህቶቻችን ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠዋል። በትልልቅ ከተሞች በተከፈቱ የራቁት ዳንስ ቤቶች ውስጥ የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ሲሉ ሕጻናት በሚያደርጉት ውዝዋዜ አዕምሯቸው በሙስና የተጨማለቀ ባለሥልጣናት


**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

መዝናኛ ሆነው የምናያቸው እህቶቻችን ሁኔታው ቢመቻችላቸውና ተምረው ለአገር ግንባታ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ ናቸው። በዐረቡ ዓለም ቤተሰብ ለመርዳት ከባርነት ባልተናነስ በቁማቸው መከራና ፍዳ የሚቀምሱ እህቶቻችን መብታቸው ተከብሮ የሥራ መስክ ቢያገኙ አላስፈላጊ የሕይወት ዋጋ መክፈል አይኖርባቸውም ነበር። ይህ እንዲያው ለምሳሌነት ተጠቀሰ እንጂ፣ የኢትዮጵያ ሴቶች የመብት ጥያቄ ጉዳይ ዳገትን፣ አቀበትንና ቁልቁለትን፣ መከራንና ስቃይን የተላበሰ መሪርና መጠነ-ሰፊ የቀን ተቀን ትግል ነው። ለዚህም "እቱ መላ ምቺ"ን የሚያዜም መላ የተላበሰ ሰፊ የሴቶችን ተሳትፎ ይጠይቃል።

ከቅድመ ታሪካችን እንደምንረዳው፣ አገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት በውጭ ወራሪ ኃይሎች በርካታ ጦርነቶች ተካሂደውባት፣ በስንት ውጣ ውረድ ሉዓላዊነቷን፣ ክብሯንና ነፃነቷን አስከብራ የኖረች ሀገር ናት። በነዚህ የነፃነት ተጋድሎዎች ሁሉ፣ የሴት ቅድመ-አያቶቻችን፣ የአያቶቻችንና የእናቶቻችን አስተዋጽዖ ለኅብረሰብ ዕድገትና ብልጽግና ወሳኝነት ነበረው። በምሳሌነት ለመጥቀስ ያህል፣ ገና ከፅንሱ ከ3 ሚሊዮን ዓመታት በፊት የነበረችዋ ድንቅነሽ (Lucy) ከዛፍ ዛፍ እየተንጠላጠሉ መኖርን ሊያስቀይራት የቻለው የማመዛዘንና የመላ-መምታት የአንስታይ ባህሪዋ ተነስታ በእግር የመጓዝን ጥበብ መጀመሯ ሌሎች ፍጥረታት በጊዜው ያልሰሩትን በሁለት እግር ቆሞ የመሄድን ጥበብ በሰው ልጅ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስመዘገበች ናት።

በ10ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን በመሪነት ብቅ ያለችው ዮዲት ጉዲት ምንም እንኳን የእምነት ግጭትን ያስከተከለ ጦር መሪ ብትሆንም፣ ከአክሱማዊት ዘመነ-መንግሥት በኋላ ለብዙ መቶ ዓመታት የኢትዮጵያን አስተዳደር የተረከበውን የዛጉዌ ሥርወ-መንግሥትን የመሠረተች የወጣላት የጦር መሪ ነበረች። ወደ 13ኛው ምዕተ-ዓመት ስንጓዝም፣ የንጉሥ ላሊበላ ባለቤት ንግሥት መስቀላ-ክብራ ሃይማኖትንና ፖለቲካን አጣምራ የያዘችና ክብር ያላት ኢትዮጵያዊት ነበረች። ከባሏ ህልፈት በኋላም፣ ቀውጢ ጊዜ ስለነበረ በአገር ጉዳይ ላይ እጇን አጣምራ በመቀመጥ ፋንታ፣ በተከታታይ ለሦስት መንግሥታት በአማክሪነት ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ስልትን የተላበሰ የፖለቲካ አመራር ከተጫወቱት ሴቶች ውስጥ አንዷ ናት። የንጉሥ ሰርፀ-ድንግል ባለቤት ልዕልት ሰበለ-ወንጌልም እንደዚሁ።

ከጥንት ጀምሮ የውጭ መንግሥታት አገራችንን ለመውረር ከመዶለት አርፈው አያውቁምና በቀጥታ በራሳቸው ሂደት ዓላማችውን ማሳካት ሲያቅታቸው እንደኃይለ ሥላሴ ጉግሳ ዓይነቱን አገር-በቀል ጠላት ማፍራት የኖረ ስልታቸው ነበር፤ ነውም። በአፄ ልብነ-ድንግል ዘመንም፣ ቱርኮች ኢማም አህመድ ኢቢን ኢብራሂምን (ግራኝ መሐመድን) ከአዳል ክልል ቆስቁሰው አነሳስተው፣ በአገራችን የሃይማኖት ጦርነት እንዲነሳ በአደረጉ ጊዜ፣ በሁለቱም እምነቶች ዙሪያ በንጉሥ ገላውዲዎስ ባለቤት በልዕልት ሰበለ-ወንጌልና በግራኝ መሐመድ ባለቤት በወ/ሮ ደል ዋምብራ የጋራ ምክክር ለአስራምስት ዓመታት የተካሄደውን እልህ አስጨራሽ ሕዝብ ያፋጀ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተካታዮች ጦርነት እልባት እንዲያገኝ ከመደረጉም በላይ፣ ለውጭ ወራሪዎችን በር ዘግቷል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የእነዚህ ሁለት አስተዋይ ሴቶች መላ-ምት ከምንም በላይ አገርን የማስቀደምን ግዴታና ኃላፊነት ለተከታይ ትውልድ አስተምረዋል። በአሁኑ ጊዜ እምነትን አስመልክቶ ላንጃበበብን ጉዳይ፤ የእነሱ አርአያነት ትልቅ ትምህርት ነውና ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅብናል!

የማያባራው የአገራችን ችግር በ18ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ምንትዋብን፣ በ19ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ደግሞ ጣይቱ ብጡልን የመሰሉ የሴት መሪዎችንም አፍርቷል። ጣይቱ፣ የነጮችን የተንኮል ሴራ አመጣጥ አስቀድማ እየተገነዘበች ለባለቤቷ ለአፄ ምኒልክ ቀንዲል ሆና የኖረች መንፈሰ ብርቱና ወደር የለሽ አርበኛ ነበረች። ለዚህም ትሩፋቷ ታሪካዊውን የአድዋን ድል ማስታወስ በቂ ነው። ያ የእሷ መላ-ምት ዛሬ የምንኮራባትን ከአፍሪካ አገሮች ሁሉ ኢትዮጵያ ለቅኝ-ግዛት ያልወደቀች ብቸኛ ነፃ አገር እንድትሆን አድርጋለች።

ከላይ የተጠቀሱ ሴት ጀግኖቻችን ሁሉ ቀደም ሲል በአገራችን የውጣ ውረድ ዘመን በአመራር ደረጃ ለአስመዘገቡት ድንቅ ሥራ የሚጠቀሱ ናቸው ለማለት ያህል እንጂ፣ መከራና ፈተና ተለይቷት የማታውቀው እናት አገራችን ዳር ድንበሯ እንዳይደፈርና ሉዓላዊነቷ እንዳይታጣ የአገር በደል በደረሰ ቁጥር ከጀግና ወንድሞቻቸው ጎን ተሰልፈው የተዋደቁላት እናቶቻችንና እህቶቻችን ብዛት ቁጥር ስፍር የለውም።

የእነዚህ ቀደምት ጀግና ሴቶች ተከታይ ትውልድም እጁን አልሰጠም፤ አይሰጥምም! በደርግና በህወሓት ዘመንም በርካታ ጀግና የጣይቱ ልጆች ተፈጥረዋል። በደርግ ጊዜ

ታሪክ የማይዘነጋቸው ጓዲቶቻችን ኢሕአፓን ተቀላቅለው ከፋሺስቱ የደርግ ጋር ሲታገሉ የወደቁ እጅግ በርካታ ናቸው። ብረት አንግበው ከወንድ ጓዶቻቸው ጋር ረሃቡንና ጥማቱን ተቋቁመው በአገራችን ጋራና ሸንተረር በመውጣትና በመውረድ ለዴሞክራሲያዊ መብት ታግለዋል፤ ብዙ መስዋዕትነትም ከፍለዋል። በከተማና በገጠር ሴቶችን በማንቃትና በማደራጀት መብታቸውን እንዲያውቁ አድርገዋል። አሁንም በኢሕአፓና በሌሎች የፖለቲካና የሲቪክ ድርጅቶች አማካኝነት የሕዝብ መብቶች እንዲከበሩ የሚታገሉ እህቶቻችን በርካታ ናቸው።

አገራችን በብዙ ሺህ ዘመኗ አያሌ ችግሮችን ተጋፍጣ ምን ጊዜም ቢሆን በድል አድራጊነት ስትወጣ የኖረች አገር ብትሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ የተጋረጠባት ችግር ግን ከሁሉም በላይ ብሔራዊ ሕልውናዋን፣ የሕዝቧን አንድነትና ደህንነት የሚነካ በመሆኑ ከምን ጊዜም በላይ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ወድቃለች። የውጭ ኃይሎች ሲመኙት የኖሩትን፣ ነገር ግን እስከዛሬ ሳይሳካላቸው የቆየውን ኢትዮጵያን የመበታተንና የማዳከም፣ ከዚያም በቅኝ ግዛታቸው ሥር የማድረጉን የረጅም ጊዜ ህልማቸውን እውን ለማድረግ አገር-በቀል፣ የእናት ጡት ነካሽ የሆኑ ጥቂት ጠባብ ጎሰኞችንና ሆድ-አደር የፖለቲካ ደላላዎችን በመጠቀም አገር የመበታተን ሤራቸውን እውን ለማድረግ እየተሯሯጡ ነው።

በመሆኑም ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፪፰ (March 8, 2016) ዓ. ም ስንዘክር፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ለእኩልነት ለመብት መከበር የሚያደርጉት ትግል የዴሞክራሲያዊ ትግል አካል ነውና፣ መልስም ሊያገኝ የሚችለው የዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ሲከበሩና የአገር ሕልውና ሲኖር ብቻ በመሆኑ፣ ቀደምት ኢትዮጵያውያት ለአገራችን ታሪክ፣ ሕልውና፣ ክብርና ነፃነት እንደተዋደቁት ሁሉ፣ ዛሬም ሌላ ፈታኝ ወቅት ላይ ነንና "ጥርስና ከንፈር ሲደጋገፍ ያምር" እንዲሉ መላ ኢትዮጵያውያት ከጀግና ወንድሞቻቸው ጎን በመቆም ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ይላል የኢሕአፓ (አንድነት)። ሴቶች የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል ናቸውና ለመብቶች መከበርና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ እህቶቻችንን እስካልታቀፉ ድረስ ምን ጊዜም ጎደሎ ነው። ስለዚህ ትግላችን እናቶችን፣ እህቶችንና ወጣት ሴቶችን ያቀፈና የደገፈ፣ የሕዝብ ደህንነትን፣ አገራዊ ሕልውናንና ሏዓላዊነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን ብቻ ነው ትግላችን

**P.O.Box 91384** **Phone: 202- 241 2078**
**Los Angeles, CA 90009** **Email Address: eprp-democratic@eprp-ihapa.com**

ግቡን የሚመታው። በመሆኑም የኢትዮጵያውያ ሁሉ መብቶች የተከበሩባት ኢትዮጵያን ዕውን ለማድረግ በጋራ እንታገል!

ኢትዮጵያ በክብርና በነፃነት ለዘላለም ትኖራለች!

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**
**Email Address**: **eprp-democratic@eprp-ihapa.com**